የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፪ ቀ ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.21
ADDIS ABABA ,22nd December,2015

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፱/፪ሺ፰

የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ………………ገጽ ፰ሺ፯፻፳፭

Council of Ministers Regulation No.369 /2015

Ethiopian Trading Businesses Corporation Establishment,Council of Ministers Regulation………………………………..page 8725

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፱/፪ሺ፰ ዓ.ም**

## የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፱/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ) የፌደራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 369/2015**

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN TRADING BUSINESSES CORPORATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916 /2015 and Article 47(1) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Trading Businesses Corporation Establishment, Council of Ministers Regulation No.369/2015".

**2. Establishment**

1/ The Ethiopian Trading Businesses Corporation (hereinafter referred to as the "Corporation") is hereby established as a Federal Government Public Enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**፫.ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የንግድ ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

**፬.ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፭.ዓላማ**

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው:-

፩/ የተመረጡ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችንና፣ መሠረታዊ ሸቀጦችን ከአገር ውስጥ እና ከውጭ አገር በተወዳዳሪ ዋጋ ገዝቶ በማሠራጨት የአገር ውስጥ ገበያን ማረጋጋት፤

፪/ ሰብል፣ አትክልት እና ፍራፍሬ በተመረጠ አኳኋን ማስመረት፣ መግዛትና ማሰራጨት፣ ክምችት መያዝ፣ ለሀገር ውስጥና ለውጪ ገበያ ማቅረብ፤

፫/ በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ግዥዎችን መፈፀምና መሸጥ፤

፬/ የአርሶ አደሩ የማምረት ፍላጎት እንዲያድግ ለግብርና ምርቶች አስተማማኝ ገበያ እንዲፈጠር እገዛ ማድረግ፤

፭/ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሠፈነበት የግብይት አሠራር መዘርጋትና መፈፀም፤

፮/ ለሥራው የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የምርምር፣ የትምህርትና የስልጠና ተቋማት ጋር መተባበር፤

፯/ የሀገር ውስጥና አለም አቀፍ ግዥዎችን በሚመለከት የምክር አገልግሎት መስጠት፣ የውክልና ግዢ መፈፀምና ሥልጠና መስጠት፤

**3. Supervising Authority**

The Ministry of Trade shall be the supervising authority of the Corporation.

**4. Head Office**

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branche offices elsewhere in other parts of the country, as may be necessary.

**5. Purposes**

The purposes for which the Corporation is established are:

1/ to purchase selected agricultural and industrial products and basic commodities from both local and foreign markets competitively and as such to stabilize domestic market;

2/ to cause selective production of agricultural crops, fruits and vegetables; buy, distribute and maintain stock and sell to domestic and foreign market;

3/ to purchase and sell products in domestic and foreign markets on the basis of prevailing market prices;

4/ to provide support to motivate farmers with a view to raise their interest to produce agricultural products and ensure that agricultural products get reliable market;

5/ to instill and operationalize modern, efficient, effective, responsible and accountable trading systems;

6/ to cooperate with concerned research, educational and training institutions to have skilled manpower in the required quantity, field of expertise and quality required for its operations;

7/ to provide consultancy, procurement and training services on national and international procurements;

፰/ የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ቦንድ የመሸጥ፣ የመግዛት፣ በዋስትና የማስያዝ፤ ከሀገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

፱/ ከተቆጣጣሪው ባለስልጣን በሚሰጠው አቅጣጫ ላይ በመመሥረት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የሰው ኃብት፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዘመናዊ ስራ አመራር ግብዓቶችን ለማግኘት የሚያስችለው ኢንቨስትመንት መሳብም ሆነ በኢንቨስትመንት ላይ መሳተፍን ጨምሮ ጥናት በማካሄድ ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤

፲/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት፡፡

## ፮.ካፒታል

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፫ ቢሊዮን ፰፻፴፮ ሚሊዮን (ሦስት ቢሊየን ስምንት መቶ ሰላሳ ስድስት ሚሊዮን) ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር ፱፻፶፱ ሚሊዮን ፩፻ ሺ (ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

## ፯.ኃላፊነት

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ፰.ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

## ፱.የተሻሩ ደንቦች

የሚከተሉት ደንቦች በዚህ ደንብ ተሽረዋል:-

፩/ የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፭/፪ሺ፭፤

፪/ የግዥ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፺፩፤

8/ to issue bonds for sale, buy,acquire and pledge bonds, negotiate and execute loan agreement from both local and foreign sources on the basis of the guidance given by the Ministry of Finance and Economic Cooperation;

9/ based on the direction given by the supervising authority, attract investment that may help in acquiring human resource, finance, technology and up-to-date processes of business, which in turn help the Corporation to remain active competently both in local and foreign markets; similarly, the Corporation may take part in such investment, in conducting studies, implementing the outcomes thereof; administrate investments and take part when necessary;

10 / to engage in any other related activities necessary for the attainment of its purposes.

## 6. Capital

The authorized capital of the Corporation is Birr 3,836,000,000 (Three Billion Eight Hundred Thirty Six Million Birr) of which Birr 959,100,000 (Nine Hundred Fifty Nine Million One Hundred Thousand Birr) is paid up in cash and in kind.

## 7. Liability

The corporation shall not be liable beyond its total assets.

## 8. Duration of the Corporation

The Corporation is established for an indefinite period.

## 9. Repealed Regulations

The following Regulations are hereby repealed:

1/ the Ethiopian Commercial Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 285/2013;

2/ the Procurement Service Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 46/1998;

፫/ የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፰/፲፱፻፺፱፡፡

## ፲.የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ

የሚከተሉት የመንግስት የልማት ድርጅቶች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል:-

፩/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፭/፪ሺ፭ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት፤

፪/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፺፰ ተቋቁሞ የነበረው የግዥ አገልግሎት ድርጅት፤

፫/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፰/፲፱፻፺፱ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት፤

፬/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፩/፲፱፻፹፭ ተቋቁሞ እንደገና ሰኔ ፳/፲፱፻፺፬ እንደ አክስዮን ማህበር ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አክሲዮን ማህበር፡፡

## ፲፩.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከተወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

3/ the Ethiopian Grain Trade Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 58/1999.

## 10. Transfer of Rights and Liabilities

The rights and liabilities of the following public enterprise shall be transferred to the Corporation:

1/ the Ethiopian Commercial Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 285/2013;

2/ the Procurement Service Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 46/1998;

3/ the Ethiopian Grain Trade Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 58/1999;

4/ the Ethiopian Vegetables and Fruits Share Company established under Regulation No. 131/1993 of the Council of Ministers and Subsequently re-established as a share company on June 27/2002;

## 11. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of December, 2015**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**